# የፍጥረተ ዓለም ታሪክ

## ትምህርት አንድ

## እንከን የለሽ ዓለም

(ዘፍ 1፥1 - 2፥3)

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ  አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# ማውጫ


1. **መግቢያ**

2. **የወፍ በረር ዳሰሳ**
   እስትንፋሰ መለኮት
      ተዓማኒነት
      ቅርፅ
   ዳራ
      በቅርበት መገኘታቸው
      ማወዳደር
   ዓላማ

3. **ስነ-ጽሁፋዊ አወቃቀር**
   ጨለማው ዝብርቅርቅ ዓለም
   ተስማሚዋ ዓለም
   ስድስቱ የማበጀት ቀናት

4. **ቀደምት ትርጉም**
   ጨለማው ዝብርቅርቅ ዓለም
   ተስማሚዋ ዓለም
   ስድስቱ የማበጀት ቀናት
      ከግብ ነፃ መውጣት
      ከነዓንን መውረስ

5. **ዘመነኛው ተዛምዶ**
   ምሥረታ
   እድገት
   ፍፃሜ

6. **ማጠቃለያ**

# 1. መግቢያ

ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ መኪናዬን እያሽከረከርሁ ሳለ መስመሩን ስቶ ከወጣ ባቡር ጋር ተገናኘሁ፡፡ የትም የማይንቀሳቀስ ሆኖ ተጎልቷል፡፡ ተከታትሎ ለመዝገምገም የተሠራው ባቡር ሐዲዱን ሲስት ትልቅ እንቅፋት ሆኖ መጎለት ብቻ ዕጣው ሆነ፡፡

በፍጥረት ጅማሬም፣ እርስ በእርሱ ተቀጣጥሎ ወደ እግዚአብሔር ፍጥረት ክቡር እና ድንቅ ፍፃሜ ያመራ ዘንድ የፍጥረት ፍሰት ሰንሰለት ወይም ጎዳና እግዚአብሔር መሠረተ፡፡ ነገር ግን የሰው ዘር፣ ደግሞ ደጋግሞ፣ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ የዘረጋውን ጎዳና መከተል ያቅተው ጀመር፡፡ ዓለምንም ከሃዲዷ ወጥታ፣ ዝብርቅርቋ የወጣ እንድትሆን አደረጋት፡፡

በዚህ ተከታታይ ትምህርት፣ በዓለም ታሪክ የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ስለ ዘረጋው ጎዳና እንማራለን፡፡ በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ "የፍጥረት ሥርዓት" ብለን የምንጠራው ማለት ነው፡፡ በተለምዶ የፍጥረተ ዓለም ታሪክ ብለን የምንጠራውን እና ከዘፍጥረት 1 እስከ 11 ያለውን ምዕራፍ እንዳስሳለን፡፡ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች የእስራኤል ሕዝብ በሙሴ መሪነት እንዲሄዱበት የሚፈልገውን መንገድ እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ አስቀድሞውኑ አስቀምጦት እንመለከተዋለን፡፡ በተጨማሪም የዚህም ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲሄድ የሚፈልገው በነዚያው ጎዳናዎች መሆኑንም እናያለን፡፡

የመጀመሪያ ትምህርታችን በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ባለው ክፍል ላይ የሚያተኩር ስለሆነ "እንከን የለሽ ዓለም" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚያም ውስጥ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት አድርጎ እንከን አልባ በሆነ መንገድ ቅርፅ እንዳስያዛት ያም እጅግ ደስ እንዳሰኘው ሙሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የጠቀሰበትን ምንባብ እናገኛለን፡፡

ወደፊት እንደምንመለከተው፣ ይህ አይነተኛ ኣርአያ ዓለም በሙሴ ዘመን እግዚአብሔር እስራኤልን ሊወስድ የሚፈልግበትን የፍፃሜ ዕጣፈንታ በተስፋ የሚያመለክት ናሙናውን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ደግሞ በየዘመናቱ የሚነሳውንም የእግዚአብሔር ህዝብ የሚጠብቀው ዕጣፈንታ መሆኑንም ያመለክታል፡፡ ነገሮች በመጀመሪያ ምን መልክ እንደነበራቸው የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ሕይወት አሁን ምን መምሰል እንዳለበትና በዓለም መጨረሻ የእኛ ዓለም በእርግጥ ምን እንደምትመስልም ጭምር ያሳየናል፡፡

ይህ ትምህርት በአራት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 የተመዘገበውን የፍጥረተ ዓለም ታሪክ በወፍ በረር እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ትኩረታችንን በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ባለው ላይ ጠበብ በማድረግ፣ አስቀድመን ስነ-ፅሁፋዊ አወቃቀሩን እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ፣ አወቃቀሩን መሠረት አድርገን የዚህን የዘፍጥረትን ክፍል ቀደምት ትርጓሜ እንመረምራለን፡፡ አራተኛ፣ የዚህን ምንባብ ትክክለኛ ዘመነኛ ተዛምዶ እንመለከታለን፡፡ እስኪ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 በሚገኘው አጠቃላይ የፍጥረተ ዓለም ታሪክ ወፍ በረር ዳሰሳ እንጀምር፡፡

# 2. ወፍ በረር ዳሰሳ

በመጀመሪያ ላይ ስትመለከቱት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 የዳሰስንበት አቀራረብ ያልተለመደ ዓይነት ይመስላል፡፡ ስለዚህ፣ መሠረታዊ ስልታችንን እናብራራለን፡፡ የዚህን ክፍል ምንባብ ጥናታችንን መስመር የሚያስይዙልን ቢያንስ ሦስት ሃሳቦች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ የእነዚህ ምዕራፎች እስትንፋስ መለኮትነት፣ ከእነዚህ ምዕራፎች በስተጀርባ የምናገኘው ስነ-ጽሁፋዊ ዳራ እና ሦስተኛ፣ እነዚህ ምእራፎች የተጻፉበት ዓላማ ናቸው፡፡ ከሁሉ አስቀድመን፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ዘፍጥረት ምእራፍ 1 እስከ 11 ጨምሮ እስትንፋሰ መለኮት መሆናቸውን በጽኑ እናረጋግጣለን፡፡

## እስትንፋሰ መለኮት

ስለ እስትንፋሰ መለኮት የያዝነው የወንጌል አማኝነት መረዳታችን ስለዚህ የዘፍጥረት መጽሐፍ አንጻ ሁለት ወሳኝ ገፅታዎችን ያሳስበናል፡፡ በመጀመሪያ፣ ተዓማኒነት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ፣ በዓላማ የተቀመጠው ቅርፁ ነው፡፡

### ተዓማኒነት

ቋንቋ ሊገልጠው በሚችል መጠን በጠነከረ አቋም ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እስትንፋሰ መለኮት ያለበት በመሆኑ ፍፁም ተዓማኒ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በምናጠናበት ወቅት በርካታ ታሪካዊ ጉዳዮች ወደ አደባባይ ይወጣሉ፣ ከእነዚህም ጉዳዮች ጥቂቶቹ ሙሉ በሙሉ መፍትሄ የሚገኝላቸው አይደሉም፡፡ ለአሁኑ ዓላማችን ግን እስትንፈሰ መለኮት የታሪካዊ ተዓማኒነት እንድምታ ያለው መሆኑን ያሳያል ማለት በቂ ነው፡፡

ሙሴ ይህንን የዘፍጥረት ክፍል ሲፅፍ ቀደምት ተደራሲያኑ ታሪካዊ ተዓማኒነት ያለው ክፍል እንደሆነ እንዲቀበሉት አድርጎ ነው፡፡ እንግዲህ፣ ለቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ እንደምናደርገው፣ ይህንን ክፍል በምንተረጉምበት ወቅት ታሪካዊ አድማሱን በተሳሰተ መንገድ ላለመረዳት አስፈላጊውን ጥንቃቄ እናደርጋለን፡፡ የሆነ ሆኖ፣ ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት እና ኢየሱስ ራሱም፣ የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 ታሪክ ተዓማኒ ታሪክ መሆኑን ያምኑበታል፡፡ እነዚህ ምዕራፎች በጥንታዊው ዓለም የተከናወነ እውነተኛና ተዓማኒ ታሪክ ዘገባዎች በመሆናቸው እምነት ላይ ትምህርቶቻችንም የበኩላቸውን ማዳበሪያ ያበረክታሉ፡፡

የፍጥረተ ዓለም ታሪክ ተዓማኒ መሆኑን ስናምን፣ ሙሴ እነዚህን ምዕራፎች በአንድ ለየት ያለ ቅርፅ እንዲያቀናብራቸውና ይዘታቸውን እንዲቀነብብ እግዚአብሔር እንደነዳው ዘወትር ማስታወስ ይገባናል፡፡

### ቅርፅ

እስኪ በዚህ መንገድ አስቡት፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 ከፍጥረተ-ዓለም ጅማሬ አንስቶ ከ 2000 – 1800 ዓመተ-ዓለም ድረስ እስከ ኖረው እስከ አብርሃም ዘመን ድረስ ያለውን ታሪክ ይሸፍናል፡፡ ሙሴ በእነዚህ ዐሥራ አንድ ዐጫጭር ምዕራፎች ውስጥ በዚያ የታሪክ ዘመን ከተከናወኑ ተግባራት መካከል በርካታ ክስተቶችን እንደተዋቸው ልንስማማ ይገባናል፡፡

ስለዚህ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 ለመረዳት በተመረጡ ጥቂቶች ላይ ማትኮሩንና የምዕራፎቹን አሰዳደር ልብ ልንል ይገባል፡፡ ሙሴ የፍጥረተ ዓለምን ታሪክ በዓላማ እንዴት ቅርፅ እንደሰጠው ልብ ካልን፣ ወሳኝ ለሆኑ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እንችላለን፡፡ ሙሴ እነዚህን ጥቃቅን መረጃዎች እንዲያካትት እግዚአብሔር ለምን ነዳው? ሥራውንስ በሚያከናውንበት ወቅት ሙሴ በዚህ መንገድ እንዲያዋቅረው ለምን ፈለገ?

ሙሴ ለምን በዚያ መንገድ ሥራውን እንደሠራው ለመረዳት፣ በእርሱ ዘመን የነበሩትን ስነ-ጽሁፋዊ ትውፊቶች ዳራ አስቀድመን መመልከት ይገባናል፡፡

## ዳራ

በመጀመሪያ የቅርብ ምሥራቅ ጥንታዊ የስነ-ጽሁፍ ታሪክ እኛ ለምንፈልገው ዓላማ ወሳኝ ነው ምክንያቱም ሌሎቹን የጥንታዊ ፍጥረተ-ዓለም ታሪኮች ሙሴ በስፋት ያገኛቸው ስለነበር ሲሆን፤ ሁለተኛ ደግሞ፣ ሙሴ ከጥንታዊያኑ የፍጥረተ-ዓለም ታሪክ ዘገባዎች ጋር ትውውቅ የነበረው መሆኑ ናቸው፡፡

**በቅርበት መገኘታቸው**

የከርሰ ምድር ቅርሶች ምርምሮች ስለ ዓለም አፈጣጠር የጻፈ የመጀመሪያው ሰው ሙሴ እንዳልነበር ያረጋግጣሉ፡፡ እርግጠኛ ለመናገር፣ እግዚአብሔር ሙሴን ነድቶታል፣ ስለዚህ የእርሱ ዘገባ እውነተኛ ነው፡፡ ሙሴ በጻፈበት ወቅት ግን በቅርብ ምሥራቅ የሚገኙ በርካታ አገራትና ቡድኖች ስለ ፍጥረተ-ዓለም ታሪክ ከእርሱ አስቀድመው የተለያዩ የፈጠራ ታሪኮችንና ገድሎችን ጽፈው ነበር፡፡

ከእነዚህ ጥንታዊ ምንባቦች አንዳንዶቹ በጣም ታዋቂ ናቸው፡፡ በርካታ ሰዎች Enuma Elish ወይም የባቢሎናውያን የፍጥረት ታሪክ ወይም "Tablet Eleven" of the Gilgamesh Epic ወይም የባቢሎናውያን የጥፋት ውሃ ታሪክ ስለተሰኙ ጽሑፎች ሰምተው ነበር፡፡ ስለ ፍጥረተ ዓለም ታሪክ የተለያዩ ድብልቅ ጽሁፎች በግብፅና በከነዓን ውስጥም ተጽፈው ነበር፡፡ እነዚህና ከጥንታዊው ዓለም የተገኙ በርካታ ሰነዶች ስለ ፍጥረተ-ዓለም መነሻና ስለ ጥንታዊ ታሪክ ይዘግባሉ፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ከእነዚህ ጥንታዊ የቅርብ ምሥራቅ ሰነዶች አብዛኞቹ ሙሴ በወጣትነቱ ዘመን በቅርብ የሚያገኛቸው ነበሩ፡፡ ሙሴ በግብፅ ቤተመንግሥት ውስጥ የተማረ ሲሆን ጽሁፎቹም የጥንታዊውን ዓለም ስነ-ጽሁፍ የሚያውቅ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ሙሴ እስትንፋሰ መለኮት እና እውነተኛ የሆነውን የፍጥረተ ዓለም ታሪክ ሲጽፍ፣ በጥንታዊው ቅርብ ምሥራቅ ከነበሩ ጽሁፎች ጋር በውል ይተዋወቅ ነበር፡፡

የተቀሩት የፍጥረተ ዓለም ጽሆፎች ለሙሴ በቅርበት ይገኙ እንደነበር በመረዳት፣ አሁን ደግሞ ሌላኛውን ጥያቄ እንጠይቅ፡ ሙሴ የሌሎችን ባህሎች ቀደምት ታሪክና ገድል እንዴት አስተናገዳቸው?

**ማወዳደር**

በእነዚህ ተከታታይ ትምህርቶች እንደምንመለከተው፣ ሙሴ የተቀሩትን የፍጥረተ ዓለም ታሪኮች በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መንገድ አወዳድሮ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሙሴ የቀደምት ዓለም ታሪኩን የጻፈው ስህተቱን በእውነት ለመጋፈጥ ነበር፡፡ ሙሴ ይመራቸው የነበሩ እስራኤላውያን ለሁሉም ዓይነት አምላክ የለሽ ዓለም ተፅዕኖ ተጋላጭ እንደነበሩ ልናስታውስ ይገባናል፡፡ ዓለም የተገኘችው በተለያዩ አማልክቶች ጥረትና ትግል እንደሆነ የማመን ፈተና ገጥሟቸው ነበር፡፡ የአባቶቻቸውን እውነተኛ እምነት ይክዳሉ ወይም ይህንን እውነት ከሌሎቹ መንግሥታት ሃይማኖታዊ ትውፊት ጋር ያደባልቃሉ፡፡  በበርካታ መንገዶች፣ ሙሴ ስለ ጥንታዊው ዓለም የጻፈው፣ ነገሮች ሁሉ በትክክል የተከናወኑበትን መንገድ ለእግዚአብሔር ህዝብ ለማስተማር ነበር፡፡ የሌሎችን ሃይማኖቶች ስህተት ከያህዌ አማንያን እውነታ ጋር እያስተያይቶ የማስቀመጥ ናፍቆት ነበረው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም፣ ሙሴ ይህንን የሃሰት አማልክት አፈ-ታሪክ የተጋፈጠበትን አሉታዊ ዓላማ ያሳካው ከእርሱ ዘመን ጋር የነበረውን የአፃፃፍ ትውፊት በአዎንታዊ መንገድ በመመርመር ነበር፡፡ ጽሁፎቹ በዓላማ ከተቀሩት የቅርብ ምሥራቅ ፅሁፎች ጋር የሚጣጣሙ ስለሆነ እስራኤል ሊገነዘብ በሚችልበት ዓይነት የእግዚአብሔርን እውነት ማስተላለፍ ችሎ ነበር፡፡ በሙሴ ዘገባዎችና በጥንታውያኑ ወሳኝ ምንባባት መካከል ብዙ መመሳሰል ቢኖርም፣ በቅርብ የተከናወነ የከርሰ ምድር ቅርስ ምርምር ግን ከአንድ ለየት ያለ ስነፅሁፋዊ ትውፊት ጋር ያላቸውን አስገራሚ መመሳሰል አመላክቶናል፡፡

በ1969 (እ.አ.አ) Atrahasis: The Babylonian Story of the Flood በተሰኘ ርእስ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ታትሞ ነበር፡፡ ይህ ሰነድ ምንያህል ርቀት ወደ ኋላ ያሉትን ዘመናት እንደሚዳስስ በእርግጠኝነት

ባናውቅም፣ ለእኛ እጅግ ወሳኝ ነው ምክንያቱም ከዚያ ቀደም በተናጠል ይታወቁ የነበሩ የተበታተኑ ታሪኮችን በአንድ ጥራዝ ያስቀመጠልን በመሆኑ ነው፡፡

የAtrahasis Epic ሦስት መሠረታዊ አወቃቀሮችን ይከተላል፡ በሰው ዘር አፈጣጠር ይጀምራል፡፡ የሰው ዘር አፈጣጠርም ቀደምት የሰው ዘር ታሪክን ያስከትላል፣ በተለይ የሚያተኩረውም በሰው ዘር ምክንያት ስለ ረከሰችው ዓለም ነው፡፡ በስተመጨረሻም፣ ይህ ርኩሰት በጥፋት ውሃ ፍርድ የተወገደ እና አዲስ የዓለም ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ያሳያል፡፡

Atrahasisን ከዘፍጥረት ጋር ስናነፃፅረው ሙሴ ዘገባውን በዓላማ በተቀናበረ ሁሉን ገዢ አወቃቀር ያደራጀው የመሆኑን ሃሳብ በብርቱ የሚደግፈው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመለከተው፣ ዘፍጥረት 1 እስከ 11 ያለው ክፍል ይህንም ያህል ብርቱ ቁርኝት የሌለውና ዝም ብሎ ከአንዱ ርዕስ ወደሌላው የሚሸጋገር ይመስላል፣ ሆኖም ከAtrahasis ጋር ያለውን ሰፊ ስነ-ፅሁፋዊ ጉድኝት ስንመለከት ግን የሙሴ የፍጥረተ ዓለም ታሪክ በአንድ ገዢ አወቃቀር የተቀናበረ ወጥ ታሪክ መሆኑን እንድናስተውል ያግዘናል፡፡

ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 በሦስት ይከፈላል፡ በመጀመሪያ ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ድረስ ያለው የፍጥረት ታሪክ፤ ሁለተኛ ከዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 4 እስከ ምዕራፍ 6 ቁጥር 8 የሚገኘው በሰው ዘር ምክንያት የዓለም እርኩሰት እና በስተመጨረሻም ከዘፍጥረት ምዕራፍ 6 ቁጥር 9 እስከ ምዕራፍ 11 ቁጥር 9 የሚዘልቀው የጥፋት ውሃና የአዲሱ ሥርዓት ዘገባ ናቸው፡፡

አሁን ደግሞ ሦስተኛውን ጥያቄ እንጠይቅ፡ ሙሴ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 ለምን ፃፈ? ለእስራኤላውያን አንባቢዎቹ ማስተላለፍ የሚፈልገው ምንድን ነው?

## ዓላማ

በጣም መሠረታዊ በሆነ ደረጃ፣ እስራኤላውያን ስላለፈው ሁኔታ እውነቱን እንዲያውቁ ሙሴ ይፈልግ የነበረ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን፡፡ በዓለም ታሪክ ቀደምት ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር ምን እንደሠራ እንዲያውቁ ይፈልጋል፡፡ የሌሎቹ ሀገሮች ጥንታዊ የአማልክት ታሪኮች ህዝባቸውን ስለነዚያ አማልክት በፃፉት መሠረት ለማሳመን በዓላማ እንደተዘጋጁ ሁሉ፣ ሙሴ ደግሞ እስራኤላውያንን ስለ እምነታቸው ታሪካዊ እውነታ ሊያሳምናቸው ብርቱ መሻት ነበረው፡፡

ጠለቅ ያለ ምርመራ በማድረግ ከሙሴ የፍጥረተ ዓለም ታሪክ በስተጀርባ ያለውን ተጨማሪ ዓላማ እንመለከታለን፡፡ በተለይም ደግሞ፣ እስራኤላውያንን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ለማጣጣም እንደጻፈ እንመለከታለን፡፡ እንግዲህ፣ ይህ ተጨማሪ ዓላማ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 ለሚያነብብ ሰው ዝም ብሎ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፣ ሆኖም ሌሎቹም የፍጥረተ ዓለም ታሪኮች ይህንን ተመሳሳይ ዓላማ የሚጋሩ መሆናቸውን ስናውቅ ነገሩ ግልፅ ይሆንልናል፡፡

የፍጥረተ ዓለም ዘገባዎችን ዓላማ ከመረዳታችን አስቀድሞ፣ በርካቶቹ የቅርብ ምሥራቅ ባህሎች ፍጥረተ-ዓለም በልዕለ ተፈጥሮአዊ የስነ-ፈለክ ጥበብ የተዋቀሩ ወይም ቅርፅ ያያዙ መሆናቸውን ያምኑ እንደነበር ልናስተውል ይገባል፡፡ ፍጥረተ-ዓለም ትርጉም በሚሰጥ መንገድ የሚንቀሳቀሰው በመለኮታዊ ትዕዛዝ መሠረት ነው፡፡ ስለዚህም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለ የትኛውም ሰው፣ ከንጉሡ አንስቶ እስከ ባሪያው ድረስ፣ ከዚህ መለኮታዊ ሥርዓት ጋር መጣጣም ይገባዋል፡፡

ታዲያ ይህ ነገር ከጥንታውያኑ የቅርብ ምሥራቅ የአማልከት ታሪኮችና ፈጠራዎች ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር አለ? በእስራኤል አቅራቢያ የሚገኙ ባህሎች ሁሉ በመጀመሪያ አካባቢ ስለ ተከናወኑ ተግባራት የሚያወሱ የፍጥረተ-ዓለም ዘገባዎች አሏቸው፡፡ ይህንንም የሚደርጉት አማልክቱ ጥንት በዓለም ላይ ያዋቀሯቸውን ነገሮች በውል ለማብራራት ሲሉ ነው፡፡ ስለ ፍጥረተ-ዓለም ወቅቶች የሚነገሩ

ትውፊቶቻቸውም ዓላማ ስለ ቀደምት የዓለም ታሪክ ባዶ ዘገባ ማቅረብ ብቻም አልነበረም፡፡ የፍጥረተ ዓለምን ጥንታዊ ታሪክ የፃፉት በወቅቱ ያለውን የሃይማኖትና የማኅበረሰብ ፕሮግራም ይሁንታ ለማሰጠት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ቀሳውስት የሆኑት፣ የእነዚህ ምንባቦች ጸሐፍት፣ በእነርሱ ዘመን ነገሮች ሁሉ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ይሆኑ ዘንድ አማልክቶች ዓለምን አስቀድሞውኑ ሥርዓት ያስያዙበትን መንገድ አመልክተዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለየት ባለ መንገድ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ማለትም እንደ መቅደስ፣ ቀሳውስትና ሥርዓቶች በመሳሰሉት ላይ ያተኩራሉ፡፡ የትኛው መቅደስ እና የትኛውስ የካህናት ቤተሰብ ለአገልግሎት ሞገስ አግኝቶ ነበር? በሚለው ላይ ያተኩራሉ፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ሰፋ ስላለው ማኅበረሰባዊ አወቃቀር ማለትም ስለ ፖለቲካ ስልጣንንና ህግጋት ትኩረት ይሰጡ ነበር፡፡ ንጉሡ ማን ነበር? አንዳንዶቹ ሰዎች ለምን ባሮች ሆኑ? የሚሉትን ይዳስሱ ነበር፡፡ ስለዚህ የአማልክት ታሪኮቻቸው፣ አማልክቱ ለፍጥረተ ዓለሙ ካስቀመጧቸው ስርዓቶች፣ አወቃቀሮች ጋር እንዲጣጣሙ ለህዝባቸው ጥሪ የሚያቀርቡባቸው ናቸው፡፡

በዚህ ትምህርት እንደምንመለከተው፣ ሙሴም ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 የጻፈው በተመሳሳይ ዓላማ ነው፡፡ በአንድ በኩል፣ ሙሴ የፍጥረተ ዓለም ታሪኩን የጻፈው ያህዌ በጥንታዊው ዘመን ዓለምን በፈጠረበትና ሥርዓት ባስያዘበት መንገድ ላይ ትኩረት በማድረግ ነበር፡፡ ከረጅም ዘመናት በፊት ነገሮች ስለተከናወኑበት መንገድ ለማስረዳት ከፍጥረት እስከ ባቢሎን ግንብ ባለው ክፍል ውስጥ ሙሴ ለእስራኤል አሳይቷል፡፡ ይህንን ያደረገው ግን ታሪካዊ ዘገባ ማቅረብን ብቻ ዒላማ አድርጎ አልነበረም፡፡ ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ወደ ከነዓን ምድር ሲመራቸው፣ የእስራኤልን ልጆች በተሳሳተ መንገድ እንደመራቸው የሚያምኑ ተቃዋሚዎች ገጥመውት ነበር፡፡ ሙሴ ለእስራኤል የነደፋቸው ፖሊሲዎችና ግቦች እግዚአብሔር ለፍጥረተ ዓለሙ ካዘጋጀው ጋር የሚጣጣም መሆኑን የፍጥረተ ዓለም ታሪክ ይገልጣል፡፡ ይህም ለተቃውሞው ምላሽ ይሆናል፡፡ ይህም በመሆኑ፣ የሙሴን ፕሮግራም መቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት መቃወም ነበር፡፡

በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ውስጥ በተቀመጠው እውነተኛ የፍጥረት ዘገባ ውስጥ፣ እስራኤል በእርግጠኝነት እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላት ተስማሚ ምድር ወደ ከነዓን እየተጓዘች መሆኑን አሳይቷል፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 4 እስከ ምዕረፍ 6 ቁጥር 8 ባሰፈረው የዓለም እርኩሰት ዘገባ ውስጥ ደግሞ፣ ግብጽ የርኩሰትና የመከራ ስፍራ መሆኗን እና የእግዚአብሔር ፍርድ በኃጢአት ላይ የሚመጣ መሆኑን ሙሴ አመልክቷል፡፡ በመጨረሻም፣ የጥፋትን ውሃና አዲስ ሥርዓት መዘርጋቱን ባመለከተበት በዘፍጥረት 6 ቁጥር 9 እስከ ምዕራፍ 11 ቁጥር 9 ውስጥ፣ ልክ ኖህ ለዓለም በረከትንና አዲስን ሥርዓት እንዳመጣ ሁሉ፣ እርሱም እነርሱን ወደ በረከትና ወደ አዲስ ሥርዓት እያስገባቸው መሆኑን ሙሴ አሳይቷል፡፡ እነዚህ የፍጥረተ ዓለም እውነታዎች ሙሴ ለእስራኤል የወደፊት ያስተዋለውን ነገር ትክክለኝነት ያረጋግጣሉ፡፡ እስራኤልን በእነዚህ እውነቶች ካሳመነ፣ ከእስራኤል መካከል ታማኝ የሆኑቱ ከግብጽ በመውጣት ከነዓንን እንደ መለኮታዊ ውርሳቸው ይወርሷታል ማለት ነው፡፡

አሁን እንግዲህ ስለ ፍጥረት ዓለም ታሪክ የሚዘግበውን የዘፍጥረት 1 እስከ 11 ጠቅለል ባለ መንገድ ካቀረብን፣ በዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያ አንጓ ውስጥ የተከናወኑትን ቀደምት ተግባራት በዝርዝር ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ ይህም በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 የተቀመጠው ተስማሚ ዓለም ነው፡፡

## 3. ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር

አብዛኛዎቹ ወንጌል አማኞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የመክፈቻ ምዕራፍ በሚያስቡበት ወቅት፣ አተረጓጎሙን ስለ ከበቡት አወዛጋቢ ጉዳዮች ያስባሉ፡፡ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በመደበኛዎቹ ስድስት ቀናት ነውን? የዘፍጥረት አንድ “ቀናት” ታላላቅ ዘመናት ወይም ዓመታት ናቸውን? ወይስ ዘፍጥረት አንድ ታሪካዊ እውነትነት የሌለው፣ የእግዚአብሔር የፈጠራ እንቅስቃሴ ስነ-ግጥማዊ ዘገባ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ አስተሳሰቦች

በወንጌል አማኞች ዘንድ እንደየጎራው ተቀባይነት አላቸው፡፡ ምንም እንኳን በእኔ አመለካከት ዘፍጥረት 1 እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በዚህ ዘመን በምናውቃቸው ስድስት ቀናት ውስጥ ነው ብዬ ባምንም፣ ሁሉም መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ክርስቲያኖች ከዚህ አመለካከት ጋር አይስማሙም፡፡

በእነዚህ ትምህርቶች የዘፍጥረትን የመክፈቻ ምዕራፎች ስንዳስስ፣ እኛን ግድ የሚለን እነዚህን ስለመሰሉ ታሪካዊ ጉዳዮች ሙብሰልሰል አይደለም፡፡ በጣም የምናተኩረው በሥነ-ጽሑፋዊ ጥያቄዎች ላይ ነው፡፡ ሙሴ እነዚህን ምዕራፎች እንዴትና ለምን ፃፋቸው የሚለው ይበልጥ ይስበናል፡፡ በእነዚህ ምንባቦች ምን ዓይነት ስነ-ጽሁፋዊ አወቃቀር እንመለከታለን፣ ደግሞስ እነዚህ ውቅሮች የሙሴን ዓላማ እንድንረዳ የሚያደርጉን እንዴት ነው? የሚሉትን እናነሳለን፡፡

ይህ ምንባብ ጅማሬ፣ መካከለኛ እና ፍፃሜ ብለን የምንጠራቸው ሦስት ዐበይት እርከኖች እንዳሉት በማንሳት ልንጀምር ይገባናል፡፡

የሙሴ የፍጥረት ዘገባ የሚጀምረው በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2 ነው፡፡ የእነዚህን ጥቅሶች ይዘት "ጨለማው ዝብርቅርቅ ዓለም" ብለን ማጠቃለል እንችላለን፡፡ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 3 እስከ 31 ደግሞ የጽሑፉን ማዕከላዊ ክፍል ይይዛል፣ ይህም "ስድስቱ የመፍጠር ቀናት" ወይም "ስድስቱ ፍጥረትን ሥርዓት የማስያዝ ቀናት" ብለን የምንጠራው ይሆናል፡፡ በመጨረሻ፣ ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 እስከ 3 የሰንበት ቀን ወይም "እጅግ መልካሙ ዓለም" ብለን የምንጠራው ይሆናል፡፡

በዚህ ትምህርት ውስጥ የምናገኘውን ውቅር ሦስት አንጓዎች እንመረምራለን፣ የምንጀምረውም በጨለማው ዝብርቅርቅ ዓለም ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ እጅግ መልካሙ ዓለም የሚያወሳውን የመጨረሻውን ክፍል እንመረምራለን፡፡ በመጨረሻም፣ ስድስቱን ሥርዓት የማስያዝ ቀናት እንዳስሳለን፡፡ እስኪ አስቀድመን በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2 የተቀመጠውን ጨለማውን ዝብርቅርቅ ዓለም እንመልከት፡፡

## ጨለማው ዝብርቅርቅ ዓለም

የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 የመጀመሪያ ክፍል ስንመለከት፣ ምድር በከበባት ቅርፅ አልባነትና በእግዚአብሔር መንፈስ መካከል የሚገኘውን ወሳኝ ድንቅ ድራማዊ ውጥረት እንመለከታለን፡፡

መክፈቻ የሆነው ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2 በቁጥር 1 ላይ ርዕሱን በመስጠት መደላድሉን ያስቀምጣል ከዚያም የዓለምን የመጀመሪያ ሁኔታ በቁጥር 2 ላይ ያብራራል፡፡ እስኪ ሙሴ በምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ውስጥ ያስቀመጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> *ምድርም ባዶ ነበረች፣ አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር (ዘፍ 1፡1-2)፡፡*

ይህ ጥቅስ በጠቅላላው ምዕራፍ ውስጥ የሚዘልቀውን ድራማዊ ውጥረት ያስተዋውቀናል፡፡ በዚህ ውጥረት መጀመሪያ ጎን፣ ምድር "ቅርፅ የለሽና ባዶ ነበረች፣" ወይም በዕብራይስጡ እንደተቀመጠው፣ *tōhû wābōhû* (תֹהוּ וָבֹהוּ) (ቶሁ ቫቦሁ) ማለት ነው፡፡ ይህ የዕብራይስጥ መግለጫ ምን እንደሚል በትክክል ልንረዳው በምንችልበት መጠን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ አናገኘውም፡፡ አብዛኞቹ ምሁራን ግን ልክ በረሃና ምድረበዳ ለሰው ሕይወት የማይመች እንደሆነ ሁሉ ዓለም ሰው ሊኖርባት የማትችል፣ ለሰው ዘር ጠንቅ ነበረች ማለት እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ እናም፣ በዚህ ምንባብ መጀመሪያ ላይ፣ ዓለም ለኑሮ የማትመች፣ ጥንታዊ እና በጥልቅ ጨለማና ዝብርቅርቅ የተሞላች መሆኑን ተመልክተናል፡፡

በዚህ ድራማዊ ውጥረት ሁለተኛውን አንጓ የምናገኘው በምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ውስጥ ነው፡፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ እንደነበር" ሙሴ ጽፏል፡፡ በዚህ ስፍራ የተጠቀመበት የዕብራይስጥ ቃል

ሜራኼፌት (*merachefet* (מְרַחֶפֶת)) ማለትም "ከበላዩ መብረር" ወይም "ከበላዩ መሽከርከር" እንደማለት ነው፡፡

ስለዚህ ይህንን ድራማዊ ምስል የምንመከተው ገና በምንባቡ ጅማሬ ላይ ነው፡፡ በአንድ ወገን በምድር ላይ ቀውስን ስንመለከት፤ በሌላ ወገን ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በዝብርቅርቁ ነገር ላይ ሰፍፎ እንመለከታለን፡፡ በውጤቱም፣ ምድርን ከድኖ የነበረውን ቅርፅ አልባነትና ጨለማ ለማስወገድ እግዚአብሔር በሥራ ላይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ ድራማዊ ውጥረት በርካታ ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ምን ያደርጋል? ቀውሱስ ምን ይሆናል?

በዚህ በመጀመሪያ ጥቅስ ውስጥ የሚገኘውን ድራማዊ ውጥረት በልቡናችን ይዘን፣ በሙሴ የፍጥረት ዘገባ ውስጥ የተገለጠውንና መፍትሄ የተሰጠበትን የመጨረሻ ክፍል ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ ይህም በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 እስከ 3 የሚገኘው ነው፡፡

## እጅግ መልካም ዓለም

ይህ ክፍል የተዋቀረው ቀለል ባለ መንገድ ነው፡፡ የሚጀምረውም እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ማጠናቀቁን በሚናገረው በምዕራፍ 2 ቁጥር 1 የማጠቃለያ ሐረግ ሲሆን፣ የሚጠናቀቀው ደግሞ በምዕራፍ 2 ቁጥር 3 እግዚአብሔር በዕረፍት ላይ ሆኖ ነው፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 2 እና 3 እንዲህ ይነበባል፡

> *እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ፡፡ እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፏልና፡፡ (ዘፍጥረት 2፡2-3)*

እግዚአብሔር ወደ ሰንበት ዕረፍት መግባቱን ለዚያም ቀን ልዩ በረከትን ማዘጋጀቱንና ቀኑንም መቀደሱን፣ በሚገልጥበት ወቅት፣ በቀውሱና በእግዚአብሔር መንፈስ መስፈፍ መካከል የነበረው ውጥረት መፍትሄ ማግኘቱን እያወጀ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጨለማውን አስወግዶታል፣ የጥልቁንም ቀውስ አቃንቶታል፣ ፍፁም እንከን የለሽ ሥርዓት በያዘችውም ዓለም ደስ ተሰኝቷል፡፡ የፍጥረት ታሪክ የሚደመደመው ፍጥረተ-ዓለም እጅግ ደስ በሚያሰኝ ሰላማዊና ፍፁም ስምረት ባለበት ሁኔታ ላይ መሆኗን በሚያሳይ መንገድ ነው፡፡

ሙሴ ስለ ፍጥረተ ዓለም ያቀረበውን ዘገባ መነሻና መደምደሚያ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በተቃወሰው ዓለምና በሰፈፈው የእግዚአብሔር መንፈስ መካከል የነበረው ውጥረት እንዴት መፍትሄ እንዳገኘ የሚናገረውን መካከለኛውን ክፍል እንመለከታለን፡፡

## ስድስቱ ሥርዓት የማስያዝ ቀናት

ይህ ምንባብ በምዕራፍ 1 ከቁጥር 3 እስከ 31 በተገለጠውና በስድስቱ አስደናቂ ቀናት ዓለምን ሥርዓት በማስያዝ እግዚአብሔር ቀውሱን እንዳስወገደው ያስተምረናል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ማእከላዊ ትኩረት ይበልጥ ግልፅ የሚሆነው ሙሴ ደግሞ ደጋግሞ "እግዚአብሔርም አለ" በሚለው ሐረግ ተግባራቱን ሲያስተዋውቀን ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የዚህ ጽሑፍ ዋና ገፀ ባህርይ እግዚአብሔር በመሆኑና የእርሱ ኃያል ቃል የእነዚህ ጥቅሶች ትኩረት በመሆኑ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ቃላት እጅግ አስደናቂ ሥርዓትን በዓለም ላይ አመጡ፡፡ የእስራኤል አምላክ ዓለምን ሲፈጥር ሌሎች አማልክቶች እንደሚያደርጉት ሁሉ ብዙ ትግልና ጦር መምዘዝ አላስፈለገውም፡፡ እርሱ ተናገረ፣ ዓለምም ተገቢ ሥርዓቷን ያዘች፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ከእግዚአብሔር አፍ የወጣው

ቃል የእርሱን ኃያል ጥበብ ይገልጣል፡፡ ዓለምንም እርሱ በመረጠው መንገድ በሥርዓት አደራጃት፡፡

አብዛኞቹ ተርጓሚዎች እንደሚስማሙበት እግዚአብሔር ፍጥረትን ሥርዓት ያስያዘባቸው ቀናት በባለሦስት መንታ አንጓዎች ይከፈላሉ፡ ይህም ከ 1ኛ እስከ 3ኛ ቀናት እና ከ 4ኛ እስከ 6ኛ ቀናት ናቸው፡፡ በእነዚህ መንታ አንጓዎች መካከል ያለው ግንኙነት በበርካታ መንገዶች ተገልጧል፣ ደግሞም በርካታ የእርስ በርስ ትስስሮችም አሏቸው፡፡

ከእነዚህ ንድፎች ጋር የምንተዋወቅበት ጠቃሚ መንገድ በምዕራፍ 1 ቁጥር 2 የተጠቀሰውን የምድር መግለጫ ቀረብ ብሎ መመልከት ነው፡፡ ሙሴ ምድር ቅርፅ የለሽና ባዶ ነበረች *tōhû wābōhû* (תֹהוּ וָבֹהוּ) (ቶሁ ቫቦሁ) በማለት የተናገረውን አስታውሱ፡፡ እነዚህ አባባሎች የባለሦስቱን መንታ ቀናት ወሳኝነት ለማብራራት ይጠቅማሉ፡፡

በአንድ ወገን፣ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት እግዚአብሔር ምድር “ቅርፅ የለሽ” ከመሆኗ ጋር ተጋጥሟል፡፡ ያም ማለት፣ አንዱን ከሌላው በመለየት ለፍጥረቱ ቅርፅ በመስጠት በፍጥረቱ መካከል የሚገኙት ግዛቶች የየራሳቸውን ማንነት እንዲይዙ አድርጓል ማለት ነው፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ፣ እግዚአብሔር በመጨረሻዎቹ ሦስት ቀናት ምድር “ባዶ” ከመሆኗ ጋር ተጋጥሟል፡፡ እግዚአብሔርም የሰጠው መፍትሄ በፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል ሁሉን እንደየወገኑ በማደራጀት መሙላት ነው፡፡

እስኪ ስለ መጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት አስቡ፡፡ በአንደኛው ቀን፣ እግዚአብሔር ቀንና ሌሊትን ለየ፡፡ ገና ፀሐይ ባልነበረችበት ወቅት እንኳን፣ በጨለማዋ ዝብርቅርቅ ዓለም ላይ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን ብሏል፡፡

በሁለተኛው ቀን፣ እግዚአብሔር የምድርን ከበብ በመለጠጥ ከጠፈር በታች ያለውንና ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ለይቷል፡፡ ይህ መለኮታዊ ተግባር ዛሬ እኛ የዓለማችን ከባቢ አየር ብለን የምንጠራውን ማለትም በምድር ላይ ያለው ውሃ በሰማይ ላይ ካለው እርጥበት ጋር እንዲለያይ አደረገ፡፡

በሦስተኛው ቀን፣ እግዚአብሔር ደረቁን ምድር ከባህሩ ለየ፡፡ ውቅያኖሶች ወደ ምድር ጠርዞች ተሰበሰቡ ምድርም ተገለጠች፡፡ በደረቁም ምድር ላይ አዝርዕቶች በቀሉ፡፡ ስለዚህም በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት እግዚአብሔር ቅርፅ የለሽ ለሆነችው ዓለም ቅርፅን ሰጠ፡፡ ጨለማንና ብርሃንን እንደየወገኑ ከጠፈር በላይና ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ለየ፣ የብሱም እንዲገለጥ አደረገ፡፡

እንደ ሙሴ ዘገባ፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት ሁሉን እንደየወገኑ በመፍጠር የምድርን ቅርፅ አልባነትን ካስወገደ በኋላ፣ በሚቀጥሉት ሦስት ቀናት በእነዚያ ቅርፆች ውስጥ የተለያዩ ዝርያዎችን በማብቀል የምድርን ባዶነት አስወግዷል፡፡

እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን በሰማይ ጠፈር ላይ በማኖር በመጀመሪያው ቀን ያበጀውን ቅርፅ ሞላው፡፡ እነዚህ ሰማያዊ አካላት ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ በየወገናቸው በሰማያት ላይ ተቀመጡ፡፡

በአምስተኛው ቀን፣ እግዚአብሔር ወፎችን በአየር ላይ፣ የባህር ፍጥረታትን ደግሞ በውቅያኖስ ውስጥ አስቀመጠ፡፡ እነዚህ ዝርያዎች ደግሞ በሁለተኛው ቀን የተበጀውንና ከጠፈረ በላይና በታች ያለውን ሞሉ፡፡

በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን በደረቁ ምድር ላይ እንስሳትንና የሰውን ዘር አኖረ፡፡ እነዚህም ዝርያዎች እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን ያበጀውን ደረቅ ምድር እንዲሞሉና በባሕርም እንዲርመሰመሱ አደረገ፡፡

ሙሴ ፍጥረተ ዓለሙን በጠቅላላ በእነዚህ ሦስት ቅርፆችና በዝርያዎቻቸው ሰብስቦ አስቀመጣቸው፡፡ ቃል በቃል ስናስቀምጠው፣ በስድስት ቀናት ብቻ እግዚአብሔር ጨለማዋንና ዝብርቅርቋን ዓለም ወደ ግሩም ስርዓት አመጣት፡፡ ሥራውም እጅግ አስደናቂ ነበር እርሱም ስድስት ጊዜ፡

*"መልካም ነበር"* (ዘፍጥረት 1፡4፣10፣12፣18፣21፣25) ብሏል፡፡

የሰው ዘር በደረቁ ምድር እንዲኖር ካደረገ በኋላ፣

*"እጅግ መልካም ነበር"* (ዘፍጥረት 1፡31) ብሏል፡፡

እግዚአብሔር በሥራው እጅግ ደስ እንደተሰኘ ሙሴ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ያለው ክፍል በውል የታሰበበት፣ ውስብስብ አወቃቀር እንደያዘ እናስተውላለን፡፡ ምንባቡ የሚጀምረው በተቃወሰችው ዓለምና እግዚአብሔርም በላይዋ ሰፍፎ እንደነበር በመናገር ነው፡፡ እግዚአብሔር ለስድስት ቀናት ያህል ዝብርቅርቋን ዓለም ሥርዓት የሚያስይዝ ቃል ተናገረ፡፡ አከታትሎም፣ በሰባተኛው ቀን በዓለም ላይ ባሰፈነው ሥርዓት እጅግ ደስ ተሰኘ፣ ስለዚህ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ፡፡

ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ያለውን አቢይ ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የዚህ ምንባብ ቀደምት ትርጉም እንዴት እንደተላለፈ እንመለከታለን፡፡

## 4. ቀደምት ትርጉም

የሙሴ የፍጥረተ ዓለም ታሪክ በዓላማ የተቀረፀው የእስራኤል ነፃ መውጣትና ድል እግዚአብሔር በቀደምት የዓለም ታሪክ ውስጥ ካሰፈነው ሥርዓት ጋር ያለውን መጣጣም በማሳየት ዋጋ እንዲሰጠው ለማድረግ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ሆኖም ይህ ጥቅል ዓላማ ከምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 በተቀመጠው ምንባብ ውስጥ እንዴት ራሱን ገለጠ? ሙሴስ ለእስራኤል የሰጠውን አገልግሎት ከፍጥረት ታሪክ ጋር እንዴት አስተሳሰረው?

ሙሴ ይህንን እንዴት እንዳከናወነው የምንመረምረው በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ውስጥ የተቀመጡትን ሦስት ዋና ክፍሎች መለስ ብለን በመመልከት ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ጨለማውን ዝብርቅርቅ ዓለም እንመለከታለን፡፡ ከዚያም ፍፁም ሥርዓት ስለ ያዘችው ዓለም ወደሚናገረው የመጨረሻ ክፍል እንሸጋገራለን፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር በዓለም ላይ ሥርዓትን ወዳሰፈነበት መካከለኛ ክፍል እንመለሳለን፡፡ እስኪ አስቀድመን በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2 ስለ ጨለማው ዝብርቅርቅ ዓለም የተጻፈውን እንመልከት፡፡

### ጨለማዋ ዝብርቅርቅ ዓለም

እኛ ላተኮርንበት ዓላማ፣ የዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ወሳኝ ገፅታ በቁጥር 2 ውስጥ የተገለጠው ድራማዊ ውጥረት ነው፡፡ ሙሴ በዝብርቅርቋ ዓለምና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ውጥረት የገለጠበት አገላለፐ እየጻፈ ያለው ስለ አፈጣጠር ብቻ ሳይሆን፣ ስለ እስራኤልም ዘጸዓት እንደነበር በግልፅ ያመለክታል፡፡

በአንድ በኩል፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ውስጥ ሙሴ ምድርን "ቅርፅ የለሽ" ወይም ቶሁ በማለት እንደገለጣት ታስታውሳላችሁ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን መንፈስ "ይረብብ ነበር" ወይም በዕብራይስጡ ሜራህፌት ብሎ ገልጦታል፡፡

የዚህ ትዕይንት ወሳኝነት ይበልጥ ግልጥ የሚሆንልን ሙሴ የዚህን ድራማዊ ትዕይንት የጠቀሰበትን ምንባብ ስንመለከት ነው፡፡ በዘዳግም ምዕራፍ 32 ከቁጥር 10 እስከ 12 ውስጥ ሙሴ የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 አገላለጥ በማንሳት በእስራኤል ዘጸዓትና በፍጥረት ሥራ መካከል ወዳለው ትስስር የተደራሲያኑን ትኩረት ሲስብ ትመለከታላችሁ፡፡

> *እርሱን በምድረ በዳ፣ ባዶና ጭው ባለ በረሓ ውስጥ አገኘው፤ ጋሻ ሆነው፤ ተጠነቀቀለትም፤ እንደ ዐይኑ ብሌን ጠበቀው፡፡ ንስር ጎጆዋን በትና፣ በጫጩቶቿም ላይ እንደምትረብብ፣ እነርሱን ለመያዝ ክንፎቿን እንደምትዘረጋ፣ በክንፎቿም እንደምትሸከማቸው፣ እግዚአብሔር ብቻ መራው፤ ምንም ባዕድ አምላክ አብሮት አልነበረም። (ዘዳግም 32፡10-12)*

እነዚህ ጥቅሶች እጅግ ወሳኝ ናቸው ምክንያቱም ሙሴ በጠቅላላ ፅሁፎቹ "ቅርፅ የለሽ" ና "መርበብ" የተሰኙ አባባሎችን በድጋሚ የተጠቀመው በዚህ ስፍራ ብቻ ነውና፡፡

በቁጥር 10 ውስጥ አባባሉ "ባዶና ጭው ያለ" በሚል ቃል የተፈታ ሲሆን በዕብራይስጡ ቶሁ ማለት ሲሆን ይህም በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 "ቅርፅ የለሽ" ተብሎ ተቀምጧል፡፡ ደግሞም በቁጥር 11 "መርበብ" የተባለው ቃል ማራህፌት የተሰኘው ሲሆን፣ ቃሉ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 የእግዚአብሔር መንፈስ በጥልቁ ላይ "ይረብብ ነበር" ተብሎ ተቀምጧል፡፡

ሙሴም ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ጋር በብርቱ ለማስተሳሰር እነዚህን ሁለት ቃላት በዘዳግም 32 ውስጥ አጣምሮ ተጠቅሞባቸዋል፡፡ ግን እነዚህ ቃላት ይህንን ትስስር የመሠረቱት እንዴት ነበር? እነዚህ ቃላት በዘዳግም 32 ውስጥ የሚሰጡት ትርጓሜ ምንድን ነው?

በመጀመሪያ፣ ሙሴ "ባዶና ጭው ያለ" የሚለውን ቃል የተጠቀመው ለግብፅ ነበር፡፡ በምዕራፍ 32 ቁጥር 10 ውስጥ እንዲህ እናነብባለን፡

> *እርሱን በምድረ በዳ፣ ባዶና ጭው ባለ በረሓ ውስጥ አገኘው፡፡ (ዘዳግ 32፡10)*

በሁለተኛ ደረጃ፣ ሙሴ "መርበብ" የተሰኘውን ቃል የተጠቀመው በእስራኤል ዘንድ የእግዚአብሔርን መገኘት ምናልባትም እስራኤልን ወደ ተስፋዪቱ ምድር በመራበት ወቅት የገለጠውን የደመናና የእሳት አምድ ለማመልከት ነበር፡፡ በምዕራፍ 32 ቁጥር 10 እና 11 ውስጥ እንዲህ እናነብባለን

> *ንስር ጎጆዋን በትና፣ በጫጩቶቿም ላይ እንደምትረብብ፣ እነርሱን ለመያዝ ክንፎቿን እንደምትዘረጋ፣ በክንፎቿም እንደምትሸከማቸው፣ እግዚአብሔር ብቻ መራው፤ (ዘዳግም 32፡10-11)*

በበርካታ መንገዶች፣ ዘዳግም ምዕራፍ 32 ከቁጥር 10 እስከ 12 ያለው ክፍል ሙሴ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ላስቀመጠው ቃል ማብራሪያ የሰጠበት ነው ማለት እንችላለን፡፡ የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ሲጽፍ የነበረውን ዓላማ እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

ሙሴ በአፈጣጠርና በእስራኤል ከግብጽ መውጣት መካከል ጉድኝት ያለ መሆኑን እንዳስተዋለ እንድንረዳ ዘዳግም ምዕራፍ 32 ያግዘናል፡፡ ፍጥረትና የእስራኤል ከግብጽ መውጣት ዝብርቅርቅና ሊኖሩበት የሚያዳግት ዓለም አብረዋቸው እንደነበሩ ለማሳሰብ ሙሴ ጽፏል፡፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር በዝብርቅርቋ ዓለም ላይ ይረብብ እንደነበረ ሁሉ እስራኤልንም ከግብጽ ሲያወጣ በላይዋ ይረብብ እንደነበር ለማመልከትም ጽፏል፡፡

በፍጥረትና በዘጸዓት መካከል ከምናያቸው ከእነዚህ ጉድኝቶች ውስጥ፣ ሙሴ ስለዝብርቅርቋ ዓለም የጻፈው ለእስራኤል ስለ ፍጥረት ለመንገር ብቻ አለመሆኑን እናያለን፤ በተጨማሪም እግዚአብሔር በመፍጠር ወቅት ያከናወነው ሥራ በእርሱ ዘመን ለእስራኤል ላደረገው ነገር ማብራሪያ የሚሆን ተምሳሊት ወይም አርዓያ እንደሆነ ለማመልከት ጽፏል፡፡ እግዚአብሔር በፍጥረት ወቅት ስላከናወነው ቀደምት ሥራ ሙሴ ሲጽፍ፣ አንባቢዎቹ ከግብፅ በሚወጡበት ወቅት እርሱን ሲከተሉ ስህተት እንዳይፈፅሙ ለማመልከት ነው፡፡ ከዚህም በላይ፣ የእነርሱ ከግብፅ መውጣት ምን ያህል የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራ ውጤት እንደሆነ የፍጥረት ታሪክ ያረጋግጣል፡፡ እግዚአብሔር ልክ በመጀመሪያ እንዳደረገው ሁሉ፣ እስራኤልን ከምስቅልቅሏ ግብፅ በማውጣት ዓለምን እንደገና ሥርዓት አስይዟል፡፡ በፍጥረት ጅማሬ በፍጥረት ላይ ይረብብ እንደነበረ ሁሉ፣ አሁን ደግሞ በእስራኤል ላይ ይረብብ ነበር፡፡ የእስራኤል ከግብፅ መውጣት እግዚአብሔር በዓለም ላይ የሚፈልገውን ሥርዓት መልሶ ማምጣቱን የሚያረጋግጥ፣ እግዚአብሔር በሥራ ላይ የመሆኑ ምልክት ነበር፡፡ በሌላ ቃል ብናስቀምጠው፣ የእስራኤል ከግብፅ መውጣት ፍጥረትን እንደገና ከመፍጠር አይተናነስም፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 የጅማሬ ሥራና በእስራኤል ከግብፅ መውጣት መካከል ስላለው ጉድኝት የተመለከትነውን በልቡናችን ይዘን፣ ይህ አመለካከት እንከን የለሽ የሆነችው ዓለም በተገለጠችበት በመጨረሻው ክፍል፣ ማለትም በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ 3 ውስጥም የተረጋገጠ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

## እንከን የለሽ ዓለም

የፍጥረት ታሪክ የሚደመደመው እግዚአብሔር ወደ ዕረፍት ገብቶ መሆኑን ታስታውሳላችሁ፡፡ በዘፍጥረት 2 ቁጥር 2 እና 3 ዕረፍት ለተሰኘው ቃል የዕብራይስጡ አቻ፣ ሰንበት *shabbat* (שָׁבַת) ብለን ምንጠራው ነው፡፡ ይህም አባባል በሌላ መንገድ የፍጥረትን ታሪክ ከእስራኤል ዘፀአት ጋር የሚያያይዝልን ነው፡፡

ሙሴ እና እስራኤላውያን ሰንበት የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ በቀደምትነት የሚያመለክተው በሙሴ ሕግ መሠረት የሰንበትን ቀን በማክበር የሚጠብቁትንና ደስ የሚሰኙበትን ሁኔታ ነው፡፡ እንዲያውም፣ በዘፀአት 20 በተመዘገበው የዐሥርቱ ትዕዛዛት ዝርዝር ውስጥ፣ እስራኤል የሰንበትን ቀን የሚያከብረው በዘፍጥረት 2 እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ ለማድነቅ መሆኑን ሙሴ አብራርቷል፡፡

> *"የሰንበትን ቀን ቅዱስ አድርገህ አክብር … እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና በውስጡም ያሉትን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ፣ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና፡፡" (ዘፀአት 20 ፡8-11)*

እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ እስራኤላውያን ከዘፍጥረት ውስጥ ሲያነብቡ፣ ወዲያውኑ የዘፍጥረትን ዘገባ ከሰንበት በዓላቸውና ከዐሥርቱ ትዕዛዛት ጋር ማገናኘታቸው አይቀሬ ነው፡፡

ምንም እንኳን እስራኤላውያን በመጠኑ ሰንበትን ማክበር የጀመሩት በምድረበዳ ቢሆንም፣ የሰንበት ቀን አምልኮ በሙላት ሊከናወን የቻለው በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ እንደነበር መገንዘቡ ወሳኝ ነው፡፡ እስራኤላውያን ሰንበትን በየሳምንቱ ያከብራሉ (ይህንንም በዘፀአት ምዕራፍ 20 ቁጥር 8-11 እናገኘዋለን)፡፡ ሆኖም ሌሎችን በዓላትን ወይም ሰንበቶችንም ያከብራሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ከዘሌዋውያን ምዕራፍ 25 እንደምንረዳው በየሰባት ዓመቱ መሬታቸውን ሳይዘሩበት ጦም በማሳደር ሰባተኛውን ዓመት የሰንበት ዓመት በማድረግ ያከብራሉ፡፡ በተጨማሪም እስራኤል በየሃምሳ ዓመቱ የኢዮቤልዩ ዓመት ታከብራለች በዚያም ዕዳዎች ሁሉ ይሰረዛሉ፣ ህዝቦችም ወደ ርስቶቻቸው ይመለሳሉ፡፡ በሙሴ ሕግ ውስጥ፣ የሰንበትን ቀን በማክበር ለእግዚአብሔር የሚቀርበው አምልኮ እስራኤል በምድረበዳ በሚንከራተትበት ወቅት ይጠብቅ ከነበረው ከየትኛውም በዓል ይልቅ ብዙ ገፅታ ያዘለ ነበር፡፡

ምክንያቱም የሰንበት ቀን በሙላት ሊከበር የሚችለው እስራኤል ወደ ተስፋዪቱ ምድር ስትገባ ነበር፡፡ ሙሴ ከነዓንን የዕረፍት ምድር ወይም የዕረፍት ስፍራ በማለት ደጋግሞ ይጠቅሳታል፡፡ ለዚህም የሚጠቀመው *nuach* (נוח) ወይም *menucha* (מְנוּחָה) የተሰኙትን የዕብራይስጥ ቃላት ሲሆን፣ እነርሱም አብዛኛውን ጊዜ ከሰንበት ጋር የቅርብ ትስስር አላቸው፡፡ በበርካታ ስፍራዎች፣ ሙሴ የተስፋዪቱን ምድር የእስራኤል የዕረፍት ስፍራ በማለት የሚጠቅሳት ሲሆን በዚያም የእስራኤል ሕዝብ በስተመጨረሻው ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ነው፡፡ ለምሳሌ በዘዳግም ምዕራፍ 12 ቁጥር 10 እና 11 እንዲህ እናነብባለን፡፡

> *ይሁን እንጂ ዮርዳኖስን ስትሻገሩና አምላካችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር ስትቀመጡ፣ ያለ ሥጋት እንድትኖሩ በዙሪያችሁ ካሉት ጠላቶቻችሁ ሁሉ ያሳርፋችኋል፡፡ ከዚያም አምላካችሁ እግዚአብሔር ለስሙ ማደሪያ እንዲሆን ወደ ሚመርጠው ስፍራ፣ እኔ የማዝዛችሁን ሁሉ፦ የሚቃጠሉ መስዋዕቶቻችሁንና ሌሎች መስዋዕቶቻችሁን፣ ዐሥራቶቻችሁንና የእጃችሁን ስጦታ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር የተሳላችኋቸውን ምርጥ ነገሮች ሁሉ ወደዚያ ታመጣላችሁ፡፡ (ዘዳግም 12፡10-11)*

በዚህ ምንባብ ውስጥ የሰንበትን ምሉዕ አከባበር፣ እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ሊከናወን የሚችለው እስራኤል ወደ እረፍት ምድር ከገባች በኋላ ብቻ ነበር፡፡

ሰንበት ለሙሴ፣ ሰዎችና ቤተሰቦች ለአምልኮ አንድ ቀን ከመለየታቸው እጅግ የዘለለ ፋይዳ ያለው ነው፡፡ ሰንበት እግዚአብሔር ስሙን ባኖረበት ልዩ ስፍራ አምልኮ የሚቀርብበት እና በዓል የሚደረግበት በእረፍት ምድር የመኖር የሙሴ ራዕይ ማዕከላዊ ትኩረት የሚያገኝበት ነው፡፡ በመዝሙር 95 ቁጥር 11 እንደተጠቀሰው አንዳንዶች ወደዚያ እንዳይገቡ እግዚአብሔር የከለከላቸው ለዚህ ነበር፡

> *ስለዚህ "ፈጽሞ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ፣ በቁጣዬ ማልሁ፡፡" (መዝሙር 95፡11)*

ይህ በሰንበትና እስራኤል በተስፋዪቱ ምድር ለእግዚአብሔር በምታቀርበው ብሔራዊ አምልኮ መካከል ያለ ብርቱ ትስስር ሙሴ የፍጥረት ታሪኩን እግዚአብሔር ወደ ዕረፍት በመግባቱ ለምን እንዳጠናቀቀው ያብራራል፡፡ ልክ እግዚአብሔር ምድርን ከዘብርቅርቅነት ወደ ሰንበት እንዳሸጋገረ ሁሉ፣ እስራኤልንም ከተቃወሰችው ከግብፅ ምድር በተስፋዪቱ ምድር ወደሚያከብሩት ሰንበት መምራቱን ሙሴ ያብራራል፡፡ ሙሴ እስራኤልን የመራው ወደ እረፍት ስፍራ ወደ ከነዓን ነበር፡፡ የሙሴን ፕሮግራም የተቃወሙት እነዚያ የተቃወሙት የሰውን ዕቅድ አልነበረም፡፡ እንደ እውነቱ የተቃወሙት እግዚአብሔር ህዝቡን ፍፁም ከሆነው የፍጥረተ ዓለም አወቃቀር ጋር ለመጣጣም ያወጣውን እቅድ ነበር፡፡ ግብፅን በመልቀቅ ወደ ተስፋዪቱ ምድር መግባት፣ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ካለው እቅድ ጋር ከመጣጣም ጨርሶ ሊያንስ አይችልም፡፡

ዝብርቁ ጅማሬና በሰንበት የተጠናቀቀው የፍጥረት ታሪክ በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር ለእስራኤል ምን እንዳደረገ እውነተኛውን ገፅታ እንደሚያብራራ ከተመለከትን፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ከቁጥር 3 እስከ 31 የሚገኘውንና ፍጥረትን ሥርዓት ያስያዘበትን ማዕከላዊ ክፍል በጥቂቱ መመልከት ይኖርብናል፡፡ ሙሴ የመፍጠርን ቀናት ከእርሱ አገልግሎት ጋር እንዴት አገናኘው?

## ስድስቱ የማበጀት ቀናት

በፍጥረተ ዓለም ቀናትና በእስራኤል ዘፀአት መካከል በርካታ ግንኙነቶች ቢኖሩም፣ ከእነዚያ መካከል ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ከግብፅ ነፃ ከመውጣት ጋር ያሉ ትስስሮች፣ ሁለተኛ፣ የተስፋዪቱን ምድር የመውረስ ግብ፡፡

## ከግብፅ ነፃ መውጣት

በመጀመሪያ ደረጃ፣ እስራኤልን ከግብፅ ነፃ ለማውጣት፣ እግዚአብሔር የገለጠው ኃይል በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 የፍጥረትን ስርዓት ለማበጀት ከገለጠው ኃይል ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ በምስሉ ሌላኛ ገፅታ ደግሞ፣ እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ መቅሰፍትን በመላክ በመፍጠር ወቅት የዘረጋውን ሥርዓት ቀልብሶታል፡፡ ለምሳሌ፣ ውኆች በመጀመሪያ እንደነበሩት በሕይወት የተሞሉ ከመሆን ይልቅ፣ በግብፅ ምድር የሚገኙ ውሆች ውሃው ወደ ደም ሲለወጥ ለሞት የሚዳርጉ ሆኑ፣ ዐሦችም ሞቱ፡፡ የሰው ዘር እግዚአብሔር በመጀመሪያ እንደሰጠው በሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ላይ ከመግዛት ይልቅ፣ እንቁራሪቶች፣ ዝንቦች፣ ነፍሳቶች እና አንበጦች በግብፅ ምድር ላይ ሰለጠኑ፡፡ በመፍጠር ወቅት ተለያይተው የነበሩት ብርሃንና ጨለማ የግብፅን ምድር በቀንም በሌሊትም ጨለማ ሲውጣት ነገሩ ተገለበጠ፡፡ ምድርም ቡቃያን ከማብቀል ይልቅ፣ በረዶ፣ እሳትና አንበጣ የግብፅን ሰብል ሁሉ አጠፋ፡፡ ፍሬያማ ከመሆንና ከመባዛት ይልቅ፣ ግብፃውን እና እንስሶቻቸው በአንድነት በብዙ ቁጥር አለቁ፡፡ በእነዚህና በሌሎችም በርካታ መንገዶች፣ በግብፅ ላይ የወረደው እርግማን በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 በስድስቱ ቀናት እግዚአብሔር ዘርግቶት የነበረውን ሥርዓት ገለባበጠው፡፡ በእነዚህ የመቅሰፍት ወቅቶችች፡፡ ግብፅ ወደ ቀደመው የዝብርቅርቅ ዓለም ተመልሳ ገባች፡፡ ስለዚህ ሙሴ ያንን ምድር ቅርፅ የለሽ፣ ጭው ያለ ምድረበዳ የሚል ስያሜ በመስጠት እንዲለቅቁ እስራኤልን ቢያሳስብ አያስደንቅም፡፡

ሕይወት በግብጽ መልካም እንደ ነበር የሚያምን የትኛውም እስራኤላዊ ከሙሴ የፍጥረት ታሪክ ጋር ሊተዋወቅ ይገባዋል፡፡ በግብጽ የነበራቸው ልምምድ ግብጻውያን ራሳቸው ስለ ምድራቸው ከነበራቸው አስተሳሰብ ጋር ፍፁም የሚቃረን ይሆናል፡፡ ምድራቸው በአማልክቶቻቸው የተባረከች እንደሆነች ያምናሉ፣ ጥቂቶቹ እስራኤላውያንም ይህንን ያምናሉ፡፡ ሙሴ በግልፅ እንዳስቀመጠው ግን ግብፅ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ፍፁም ዓለም ተቃራኒ ናት፡፡

ይህ ከግብፅ ጋር ያለው ንፅፅር ግልፅ ቢሆንም፣ ስድስቱ የመፍጠር ቀናት ከግብፅ ነፃ መውጣት ጋር አዎንታዊ የሆነ ትስስር አላቸው፡፡ ምድራቸው ከጥንቱ ዝብርቅርቅ ዓለም ጋር ተመልሳ የተመሳሰለች እንደሆነ ግብጻውያን ሲመለከቱ፣ እስራኤላውያን ግን እግዚአብሔር ልክ በስድስቱ የመፍጠር ቀናት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ስለ እነርሱ ሲል ዓለምን ሥርዓት እንዳስያዘ ያምናሉ፡፡ ውሃዎቻቸው አሁንም ንፁህና ሕይወት ሰጪ ናቸው፡፡ በእንቁራሪቶችና በአንበጣዎች አይወረሩም፡፡ ግብፃውያን በጨለማ በተዋጡበት ወቅት እነርሱ በብርሃን ውስጥ ነበሩ፡፡ የእስራኤል እርሻዎች ምርታማነት እንደዘለቀ ነው፡፡ እንስሶቻቸው የተጠበቁ ናቸው፣ እስራኤላውያንም በግብፅ ውስጥ በነበሩበት ወቅት እጅግ በዝተው ነበር፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ እግዚአብሔር ፍጥረትን በመቆጣጠር አስደናቂ ተዓምራዊ ድርጊቱ፣ ልክ በመፍጠሩ ሥራው በሦስተኛው ቀን እንዳደረገው ሁሉ ቀይ ባህር እንዲሰበሰብና ደረቁ ምድር በእስራኤል ፊት እንዲገለጥ አደረገ፡፡ ስለ እስራኤል ሲል እግዚአብሔር ያከናወነው አስደናቂ

ተዓምር ማንም እንዲህና እንዲያ ብሎ ድንጋጌ ሊያወጣለት የሚችለው አልነበረም፡፡ በበርካታ መንገዶች፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እግዚአብሔር ዓለምን ሥርዓት ያስያዘበትን መንገድ የሚያሳስቡ ናቸው፡፡

በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እግዚአብሔር ምድርን ስርዓት ባስያዘበት መንገድ እና እስራኤልን ከግብፅ ነፃ ባወጣበት መንገድ መካከል ያለው ትስስር የሚያመለክተው ለሙሴ ተደራሲያን እግዚአብሔር የሠራው ሥራ ከመፍጠር ሥራው ጋር የሚጎዳኝ መሆኑን ነው፡፡ ከግብፅ ነጻ በመውጣታቸው ውስጥ፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ እንዳደረገው ሁሉ ዓለምን መልሶ ሥርዓት አስይዟል፡፡

ከግብፅ ነጻ የመውጣታቸው ነገር የፍጥረትን የጅማሬ ቀናት የሚያሳስብ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የመሠረተው ሥርዓትም በምድረ ከነዓን ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበትም የሚያሳይ ነበር፡፡

## ከነዓንን መውረስ

እስራኤል ወደ ተስፋዪቱ ምድር ስትደርስ፣ ፍጥረት በልምላሜና በደስታ ስርዓቱን ጠብቆ ይጓዝ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ከነዓንን ወተትና ማር የምታፈስስ ምድር ይላት የነበረው ለዚህ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በስድስተኛው ቀን እግዚአብሔር ደንግጎት የነበረውን የእግዚአብሔርን አምሳልነት ተገቢ ስፍራቸውን እስራኤላውያን በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ ይዘው ነበር፡፡

በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 28 ውስጥ፣ እግዚአብሔር በተለይ ለሰው ዘር የተናገረውን ልብ በሉ፡

> *"ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም፤ የባህርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው፡፡"(ዘፍጥረት 1፡28)*

ምንም እንኳን እስራኤል ገና በግብፅ ሳለች ከእነዚህ በረከቶች ጥቂቶቹን የተለማመደች ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ይህንን የመሰለ ከበሬታን ለእስራኤል ያጎናፀፈው በምድረ ከነዓን ነበር፡፡ እስራኤላውያን በፍጥረት ጅማሬ የተቀበሉትን ሥልጣን ወደሚለማመዱበት ስፍራ በሙሴ አመራር አማካይነት እየተጓዙ ነበር፡፡ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 26 ቁጥር 9 ውስጥ ታማኝ የሆኑት እስራኤላውያን በምድራቸው ሲገቡ ስለሚጠብቃቸው ነገር እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ አድምጡ፡

> *ፊቴም ወደ እናንተ ይሆናል፣ እንድታፈሩም አደርጋችኋለሁ፣ አበዛችሁማለሁ፤ ቃል ኪዳኔንም ከእናንተ ጋር አጸናለሁ፡፡ (ዘሌዋውያን 26፡9)*

በዚህ ስፍራ ዘፍጥረት ምእራፍ 1 ቁጥር 28 በተዘዋዋሪ ተቀምጧል፡፡ በዘፍጥረት 1 ቁጥር 28 ውስጥ እግዚአብሔር "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት" ብሏል፡፡ በዘሌዋውያን ምእራፍ 26 ቁጥር 9 ውስጥም በምድሪቱ ውስጥ ፍሬያማ እና በቁጥር የበዙ እንደሚያደርጋቸው ተናግሯል፡፡

የከነዓን ምድር እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሥርዓት አስይዟት የነበረችውን አስደናቂ ምድር ትመስላለች፡፡ የከነዓን ምድር የእግዚአብሔር አምሳል አስቀድሞ የተቀበለውን ሃላፊነት ማሟላት የሚችልባት ተፈጥሮአዊ ስምረት የነበረባት ምድር ናት፡፡

ስድስቱ የመፍጠር ቀናት እስራኤላውያን በሙሴ ዘመን ከገጠማቸው ነገር ጋር የነበረውን ትስስር የሚያመለክቱ ጥቂት መንገዶችን ብቻ ዳሰስናል፡፡ ሆኖም በዚህ ናሙና በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለምን እንዴት ስርዓት እንዳስያዘ ሙሴ የዘገበው በፍጥረት ጅማሬ ምን እንደተከናወነ ለመዘገብ ብቻ እንዳልሆነ ተመልክተናል፡፡ ስድስቱን የፍጥረት ቀናት የገለጣቸው እስራኤላውያን ተደራስያኑ በራሳቸው ሕይወት ውስጥ ምን እየተከናወነ እንደሆነ በግልፅ እንዲያስተውሉ ለማድረግ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለፍጥረት ሥርዓትን በማበጀት ትዕይንት ዓለምን ከዝብርቅርቅነት ወደ ሰንበት እንዳመጣ ሁሉ፣ ስለ እነርሱ ብሎ ዓለምን እንደገና ሥርዓት በማስያዝ ከዝብርቅርቋ ግብፅ በማውጣት በከነዓን ምድር ወደ ሰንበት ዕረፍት ይዟቸው ገባ፡፡

ሙሴ ስለ ዓለም አፈጣጠር ሲነግራቸው እስራኤላውያን ምን ተሰምቷቸው እንደሆነ ከመገመት በስተቀር ምንም ማድረግ አንችልም፡፡ በእነርሱ ላይ እየሆነ ያለው ነገር ድንገተኛ እንዳልሆነ ግን ይገነዘባሉ፡፡ እነርሱን ከግብጽ ባርነት በመዋጀት ወደ ከነዓነ ምድር ሲወስዳቸው፣ ልክ በመጀመሪያ እንዳደረገው ሁሉ በፍጥረተ ዓለሙ ላይ እንከን የለሽ ሥርዓት ለማስፈን እግዚአብሔር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የእስራኤል መዳን እንደገና መፈጠር ነው፡፡ ስለዚህም የዚህን የእንደገና መፈጠር በረከት በእጅጉ ለመቋደስ ሙሴን ሊከተሉ ይገባቸው ነበር፡፡

የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ድረስ ያለውን ተቀዳሚ ትርጉም ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ መጨረሻው ርእሳችን እንሸጋገራለን፡፡ እርሱም የፍጥረት ታሪክ ዘመነኛው ተዛምዶ ነው፡፡ ይህንን ምንባብ ለማዛመድ፣ በዚህ ምንባብ መሪ ሃሳቦች ላይ አዲሰ ኪዳን የሰጠውን ማብራሪያ በቅርበት እንመለከታለን፡፡

# 5. ዘመነኛው ተዛምዶ

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ስለ እግዚአብሔር የዓለም አፈጣጠር ለመናገር ዘፍጥረት ምእራፍ 1 ላይ በብርቱ ይደገፋሉ፡፡ የሙሴ ዘገባ አስተማማኝ መሆኑን ስለማመናቸው ለማረጋገጥ እያንዳንዳቸውን ፍንጮች ይዳስሳሉ፡፡ ይህ እውነታ እጅግ ጠቃሚ ሆኖ ሳለ፣ በዚህ ትምህርት ሰፋ አድርገን እንደምንመለከተው የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የሙሴንም ዓላማ ሰፋ አድርገው አቅርበውታል፡፡

ልክ ሙሴ የፍጥረትን ታሪክ የእስራኤል ከግብጽ የመቤዠት ተምሳሊት አድርጎ እንደተመለከተው ሁሉ፣ አዲስ ኪዳንም ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ድረስ ያለው ታሪክ የላቀ መቤዠት ተምሳሊት እንደሆነ አድርጎ ይመለከተዋል፡፡ ያም በክርስቶስ የሚገኘው ድነት ነው፡፡ በብሉይ ኪደን ዘመን እስራኤል የተለማመደችው መዳንና ፍርድ፣ በመጨረሻው ቀን እግዚአብሔር በልጁ፣ በኢየሱስ የሚያመጣውን ድነትና ፍርድ የሚያመለክት መሆኑን አዲስ ኪዳን ያስተምራል፡፡ ይህም እምነት የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ሙሴ ስለፍጥረት ያቀረበውን ዘገባ በልዩ ሁኔታ በክርስቶስ ላይ በማትኮር እንዲመለከቱት አድርጓቸዋል፡፡ ልክ እስራኤል የራሷን ዘፀአት በፍጥረት መነፅር እንዳየች ሁሉ፣ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍትም ወደ ክርስቶስ የተመለከቱት በፍጥረት መነፅር ነው፡፡

የአዲስ ኪዳንን ትምህርት በክርስቶስ የመቤዠት ሥራ በምንመረምርበት ወቅት ሁሉ፣ ክርስቶስ ዓለምን ሲቤዥ ሁሉን በአንድ ጊዜ ብቻ አለማከናወኑን የአዲስ ኪዳን ፀሐፍት እንደተረዱ ዘወትር ልብ ልንል ይገባናል፡፡ ይልቁኑ፣ ክርስቶስ ታላቁን ማዳኑንና ፍርዱን ወደ ዓለም ያመጣው እርስ በርስ በተሳሰሩ ሦስት የመንግሥቱ እርከኖች ውስጥ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

በመጀመሪያ፣ ክርስቶስ ለህዝቡ ድነት የሚሆነውን አብዛኛውን ነገር ያከናወነው ወደ ምድር መጀመሪያ ሲመጣ ነው፡፡ ይህንንም ወቅት የክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት፣ የመንግሥቱ ምሥረታ እንለዋለን፡፡ አዲስ ኪዳን የክርስቶስን ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤ እና እርገት ደግሞም የሐዋርያት አገልግሎት ጅማሬ እስከሆነው የጰንጠቆስጤ ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የክርስቶስ ታላቅ ቤዛነት ጅማሬ አድርጎ ይመለከተዋል፡፡

ሁለተኛ፣ ክርስቶስ አሁን ምድርን ተለይቶ በሄደበትም ወቅት መንግሥቱ ግን መቀጠሉን የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ተገንዝበዋል፡፡ በዚህ ወቅት፣ የእግዚአብሔር የማዳኑ ጸጋ በወንጌሉ ስብከት አማካይነት በመላው ዓለም ይስፋፋል፡፡ ከሐዋርያት በኋላ ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ ያለው የቤተክርስቲያን አጠቃላይ ታሪክ በክርስቶስ የተገኘው ድነት መቀጠሉን ይይዛል፡፡

ሦስተኛ፣ ድነት ፍፁም የሚሆነው፣ ክርስቶስ በክብር ተመልሶ በሚመጣበት በፍፃሜ ወቅት መሆኑን አዲስ ኪዳን ያስተምራል፡፡ በክፉዎች ላይ ድል መንሳቱን እናያለን፣ በክርስቶስ ሆነው ያንቀላፉት ይነሣሉ፣ እኛም ከእርሱ ጋር ዓለምን እንገዛለን፡፡ በክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት የተጀመረው ዛሬም እየቀጠለ ያለው ድነት በፍፃሜ ቀን ዳግም ሲመለስ ይጠናቀቃል፡፡

እነዚህ ሦስት የክርስቶስ መንግሥት እርከኖች የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ሙሴ ስለ ፍጥረት ያቀረበውን ዘገባ ያስፋፉ መሆኑን በማመልከት ረገድ ወሳኝ መሆናቸውን በመረዳት እያንዳንዳቸውን በጥንቃቄ ለየብቻ ልንመለከታቸው ይገባል፡፡ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት የሙሴን ፈለግ በመከተል፣ የዘፍጥረትን የፍጥረት ዘገባ ከክርስቶስ የማዳን ሥራ ጋር ማለትም ምሥረታውን፣ እድገቱን እና ፍፃሜውን አዛምደው አቅርበውልናል፡፡ እስኪ አስቀድመን አዲስ ኪዳን የዘፍጥረትን የመጀመሪያ ምዕራፍ ከመንግሥቱ ምሥረታ ጋር ያገናኘባቸውን መንገዶች እንመልከት፡፡

## ምሥረታ

አዲስ ኪዳን የፍጥረትን ሥርዓት የክርስቶስን መንግሥት ምሥረታ የመመልከቻ መነፅር አድርጎ ያቀረበው እንዴት ነው? አዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ጊዜ፣ ስለ ክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት ሲናገር እግዚአብሔር ፍጥረትን እንደገና ከመፍጠሩ፣ ማለትም ፍጥረተ-ዓለምን እንደገና ቅርፅ ከማስያዙ ጋር አገናኝቶ ይናገራል፡፡ አስቀድመን የዮሐንስን ወንጌል የመክፈቻ ቃላት እንመልከት፡፡ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ 3 ያሉት እንዲህ ይነበባሉ፡

> *በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፤ እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፡፡ ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሯል፤ ከተፈጠረውም ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም፡፡ (ዮሐንስ 1፡1-3)*

ዮሐንስ የጀመረው "በመጀመሪያ" በሚል ቃል መሆኑን ልብ በሉ፡፡ እነዚህ ቃላት ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 የመክፈቻ ቃል የመጡ ናቸው፡፡ ሙሴ እንዲህ ጽፏል፡

> *በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ (ዘፍጥረት 1፡1)*

ገና ከመንደርደሪያው፣ ዮሐንስ አንባቢዎቹን በዘፍጥረት ማዕቀፍ ውስጥ ያስቀምጣቸዋል፡፡ ከዚያ በመቀጠልም ዮሐንስ ክርስቶስ ሁሉን የፈጠረ የስላሴ አካል ነው ይላል፡፡ እርሱ እግዚአብሔር ዓለምን በመጀመሪያ ሲፈጥር የተናገረው ቃል ነው፡፡

ምንም እንኳ እነዚህ ጥቅሶች ከፍጥረት ታሪክ ጋር በግልፅ ተጣቅሰው ቢጀምሩም፣ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ማንበባችንን ስንገፋበት፣ ዮሐንስ ሰወር ባለ መንገድ ጉዳዩን ከፍጥረት ዘገባ ጋር ተያያዥነት ወዳላቸው ሌሎች ሁነቶች ዘወር ሲያደርገው እናገኘዋለን። በቀጣዮቹ ቁጥሮች፣ ማለትም በዮሐንስ 1 ቁጥር 4 እና 5 የጻፈውን አድምጡ፡

> *ሕይወት በእርሱ ነበረች፤ ይህች ሕይወት የሰው ብርሃን ነበረች። ብርሃንም በጨለማ ያበራል፤ ጨለማውም አላሸነፈውም። (ዮሐ 1፡4-5)*

በዚህ ነጥብ ላይ ዮሐንስ በዘፍጥረት ምእራፍ 1 መሪ ሃሳቦች ላይ ትኩረት በመስጠቱ ይገፋበታል፣ በተለይም በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር በጨለማው ዝብርቅርቅ ዓለም ላይ ባመጣው ብርሃን ላይ ያተኩራል። ሆኖም፣ ኢየሱስ የዘፍጥረቱ ብርሃን ነው ከማለት ይልቅ፣ በኃጢአት ምክንያት በጨለማ በተዋጠችው ዓለም ላይ የሚያበራ ብርሃን ነው በማለት የክርስቶስን ትስጉት ይጠቅሰዋል። ከፍጥረት ወደ ክርስቶስ መምጣት ነገሩን ዘወር በማድረግ፣ በጨለማ በተዋጠችው ኃጢአተኛ ዓለም ላይ ክርስቶስ ማብራቱ፣ ልክ በመጀመሪያ እንዳደረገው ሁሉ፣ እግዚአብሔር እንደገና በዝብርቅርቋ ዓለም ውስጥ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ዮሐንስ ያብራራል።

ተመሳሳይ የሆነው መግለጫ በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 6 ላይ ይገኛል። በዚያ ስፍራ ጳውሎስ የአገልግሎቱን ክብር እንዲህ ያስቀምጠዋል፡

> *በክርስቶስ ፊት እግዚአብሔር የክብሩን እውቀት ብርሃን ይሰጠን ዘንድ፣ "በጨለማ ብርሃን ይብራ" ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በልባችን አብርቶአልና። (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡6)*

በዚህ ስፍራ፣ ጳውሎስ በቀጥታ የሚያጣቅሰው በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 *"እግዚአብሔርም .... አለ በጨለማ ላይ ብርሃን ይሁን"* ባለው ላይ ነው። በመጀመሪያ ብርሃንን በመግለጥ ፍጥረትን በማበጀቱ ሥራ ላይ ያተኩርና፣ ወዲያው ትኩረቱን ወሳኝ ወደሆነው የፍጥረት ተዛማጅ ሃሳብ በማዘዋወር እግዚአብሔር "ብርሃኑን በልባችን አበራ" ይላል። ይህም ሆነው "የእግዚአብሔር ክብር" "በክርስቶስ ፊት ላይ" ሲገለጥ ነው።

የክርስቶስ ፊት በዓለም የተገለጠበትን ወቅት ይህም የክርስቶስ መንግሥት የተመሠረተበትን ወቅት በግሩም ሁኔታ የምንረዳው ከእግዚአብሔር የመፍጠር ታሪክ ጋር ስናዛምደው መሆኑን ሐዋርያው ይናገራል። በመጀመሪያ ብርሃንን በመግለጥ የታየው ያ የእግዚአብሔር ክብር ወደ ጨለማው ዓለም ክርስቶስ መጀመሪያ ሲመጣም ተገልጧል።

ከእነዚህ ሁለት ምንባቦች ሙሴ ስለ ፍጥረት ያቀረበውን ዘገባ በጥሩ ሁኔታ እንድንመለከተው የሚያስችሉን ክርስቲያናዊ ወሳኝ ውቅሮችን እናገኛለን። የክርስቶስ ተከታዮች በክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት፣ ማለትም በመንግሥቱ ምሥረታ ወቅት እግዚአብሔር ሊሠራ ያለውን እና የሚጠበቀውን ነገር ተምሳሊት በዘፍጥረት 1 ውስጥ ያገኛሉ።

እኔና እናንተ ሙሴን ይከተሉ የነበሩ እስራኤላውያን እንደገጠማቸው ያለ ፈተና በብዙ መንገድ ይገጥመናል። ልክ እስራኤልን ከግብጽ ነፃ ሲያወጣቸው እንደገለጠው አይነት ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምድር ሲመጣም እግዚአብሔር አስደናቂ ነገር አደርጓል። ሆኖም፣ የዛሬ 2000 ዓመት እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ምን ዐይነት አስደናቂ ነገር እንዳደረገ ማየት ይሳነናል። ምንም መረጃ ከሌለው ከሰብዓዊ ምቾት አንፃር፣ የክርስቶስ ሕይወት እምብዛም ፋይዳ

የሌለው ይመስላል፡፡ በእነዚያ ወቅቶች ተከናውነው እንደነበሩ ይህን ያህልም ፋይዳ እንደሌላቸው ነገሮች እርሱንም በቀላሉ እንዘነጋዋለን፡፡ ስለ ክርስቶስ በዚህ ዓይነት የማሰብ ፈተና ሲገጥመን፣ የአዲስ ኪዳንን አመለካከት ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ የክርስቶስ በምድር መገለጥ እግዚአብሔር ዓለምን እንደገና የማበጀቱ ጅማሬ ነው፡፡ ከኃጢአትና ከሞት አስከፊ ጨለማ እግዚአብሔር ዓለምን ነፃ እያወጣ ነው፡፡ የክርስቶስ መጀመሪያ መምጣት እግዚአብሔር ፍጥረቱን አስደናቂ፣ የዘላለም ሕይወት መገኛ እና ክብሩንም ለዘላለም የሚያኖርበት ስፍራ የማድረግ ሥራውን ሂደት የጀመረበት ነው፡፡ እምነታችንን በክርስቶስና በእርሱ ላይ ብቻ ማድረጋችን ትክክል ነው፡፡

አዲስ ኪዳን የክርስቶስን የመጀመሪያ መምጣት ወሳኝነት ለማብራራት የፍጥረትን ታሪክ እንደተጠቀመበት እስከ አሁን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ አዲስ ኪዳን የመንግሥቱን መቀጠልም ትኩረት እንደሰጠው እንመለከታለን፡፡ በክርስቶስ የመጀመሪያና የዳግም መምጣት መካከል ያለው ጊዜ፣ እንደገና የመፍጠርም ጊዜ ነው፡፡

## እድገት

ይህንን አመለካከት የሚገልጥ አንድ የተለመደ ምንባብ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 17 ነው፡፡

> *ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኗል፤ (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17)*

የዚህ ክፍል የኪንግ ጀምስ ቅጂ አንድ ሰው በክርስቶስ ሲሆን "አዲስ ፍጡር" ይሆናል ይለዋል፡፡ ይህ ትርጓሜ ጳውሎስ ከዘፍጥረት 1 ጋር ያስተሳሰረበትን ዋና ጉትት ይሸፍነዋል፡፡ የግሪኩ አገላለጥ *ktisis* (κτίσις) በትክክል ሲተረጎም "ፍጥረት" ነው እንጂ "ፍጡር" አይደለም፡፡ እንዲያውም ይህ ምንባብ አዲስ ፍጥረት ነው መባል አለበት፡፡ (አማርኛችን በዚህ ረገድ ትክክል ነው) የጳውሎስ አመለካት የሚመስለው፣ ሰዎች በሚያድን እምነት ወደ ክርስቶስ ሲመጡ የአዲስ ግዛት፣ የአዲስ ዓለም እና የአዲስ ፍጥረት አካል ይሆናሉ የሚል ነው፡፡

በዚህ ብርሃን መሠረት በመንግሥቱ እድገት ወቅት ወንዶችና ሴቶች እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ሲያሳርፉ የአዲስ ፍጥረት በረከትን እንደሚቋደሱ እንመለከታለን፡፡ በዚህ መሠረት፣ ስለ ክርስቶስ በሰማ፣ ባመነ እና በሚከተል ሰው ሕይወት ውስጥ ምን እንደተከናወነ በትክክል ለመረዳት የዘፍጥረት ዘገባ ወሳኝ ነው ማለት ነው፡፡ እኛ የእግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት አካል ስንሆን፣ እግዚአብሔር በእንከን የለሽ ዓለም ውስጥ የዘረጋው አስደናቂ ሥርዓት በረከት ተቋዳሽ እንሆናለን፡፡

በዚህ ምክንያት፣ ጳውሎስ የአንድን ሰው የድነት ሂደት በሌላ መንገድ ከዘፍጥረት ዘገባ ጋር አገናኝቶ መግለጡ አያስደንቀንም፡፡ በቆላስይስ ምእራፍ 3 ቁጥር 9 እና 10 ውስጥ እንዲህ እናነብባለን፡

> *አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር አውልቃችሁ ስለ ጣላችሁ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፡፡ የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል በእውቀት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል፤ (ቆላስይስ 3፡9-10)*

በዚህ ምንባብ ውስጥ፣ እንደ ዘፍጥረት 1 አገላለጥ በክርስቶስ ተከታዮች ውስጥ ምን እንደተከናወነ ሐዋርያው ይገልጣል፡፡ እኛ "የፈጣሪችንን መልክ እንድንመስል ተለውጠናል"፡፡ ጳውሎስ ያጣቀሰው ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 27 ሲሆን በዚያም ሙሴ የሚናገረው የእግዚአብሔር እንከን የለሽ ዓለም "በእግዚአብሔር አምሳል" የተፈጠሩትን አዳምንና ሔዋንን የሚያካትት መሆኑን ነው፡፡

በክርስቶስ መንግሥት እድገት ጊዜም፣ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን የእግዚአብሔር አምሳል እንደነበረባቸው ሁሉ እኛም ያንን ደረጃ መልሰን እስከንይዝ ድረስ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ "እንለወጣለን"፡፡

አዲስ ኪዳን የሙሴን የፍጥረት ዘገባ የክርስቶስን ሥራ በጅማሬው ብቻ ሳይሆን በእድገቱም ወቅት የሆነውን የምንገነዘብበት ሚዛን አድርጎ እንደሚያቀርብን እነዚህ ሁለት ምንባቦች ያሳያሉ፡፡

የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት የሙሴን የፍጥረት ታሪክ መሪ ሃሳቦች ከአንድ የመጨረሻ እርከንም ጋር ያገናኙልናል፡፡ የክርስቶስን የመጀመሪያ መምጣት የአዲስ ፍጥረት ጅማሬ መሆኑን ብቻ ደግሞም በመንግሥቱ እድገት ወቅት እያንዳንዱ ሰው የአዲስ ፍጥረትነትን በረከት የሚቋደስ መሆኑን ብቻ አያሳዩንም፣ ይልቁኑ በመንግሥቱ ፍፃሜ ወቅት የሚሆነውን የክርስቶስን ሥራም ከፍጥረት መሪ ሃሳቦች ጋር ያዛምዱልናል፡፡

## ፍፃሜ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በዚህ ረገድ የሚጠቀሱ ቢያንስ ሁለት ምንባቦች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 የክርስቶስን መመለስ ከሙሴ የፍጥረት ዘገባ ጋር ያጣቅሰዋል፡

> *ስለ ሰባተኛውም ቀን በአንድ ስፍራ፣ "በሰባተኛውም ቀን እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ዐረፈ" ብሎአልና፡፡ ... ስለዚህ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ቀርቶለታል፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የሚገባ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፣ እርሱም ደግሞ ከሥራው ያርፋል፡፡ እንግዲህ ... ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ፡፡ (ዕብራውያን 4፡4-11)*

ልክ ሙሴ በዘፍጥረት 2 የጠቀሰውን የእግዚአብሔርን ዕረፍት እስራኤልን ወደ ዕረፈታቸው ስፍራ ወደ ከነዓን እንዲገቡ ለማበረታታት እንደተጠቀመበት ሁሉ፣ የዕብራውያንም ጸሐፊ የእግዚአብሔርን ሰንበት ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ የምናገኘው የፍፃሜ መቤዠት ዐይነተኛ ተምሳሊት አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ዓለምን ሁሉ አበጃጅቶ የሰንበትን ደስታ እንዳመጣ ሁሉ፣ ክርስቶስም ዳግም በክብር ሲመጣ ዓለምን እንደገና ያበጃጃታል የእርሱ የሆኑትንም ወደ ዘላለም የሰንበት ዕረፍት ይዞ ይገባል፡፡ ያንን ቀን በናፍቆት ስንጠባበቅ፣ ክርስቶስ ሲመለስ ወደምንቀበለው "ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንድንተጋ" በዚህ ክፍል ተነግሮናል፡፡

በመጨረሻ፣ የክርስቶስን ዳግም ምፅዓት ከሙሴ የፍጥረት ዘገባ ጋር የሚያመሳስልልን አስደናቂ ምንባብ በራእይ 21 ቁጥር 1 የተጠቀሰው ነው፡፡ ዮሐንስ የፍጥረትን መሪ ሃሳቦች ከክርስቶስ መመለስ ጋር እንዴት እንሚያዛምዳቸው አድምጡ፡

> *ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፣ ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም፡፡ (ራእይ 21፡1)*

ዮሐንስ ስለ "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር" ይናገራል፣ ይህም ሐረግ እግዚአብሔር "ሰማይንና ምድርን" መፍጠሩ የተመዘገበበትን ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 መለስ አድርጎ ያስቃኛል፡፡ ከዚያም ባሻገር ዮሐንስ ""ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም" ይላል፡፡ ይህንንም ስታነብቡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 9 እግዚአብሔር ባሕሩን ሰብስቦ፣ ድንበር ሲያበጅለትና ደረቁም ምድር ለሰው ዘር መኖሪያነት ምቹ ሆኖ እንዲገለጥ ማድረጉን ታስታውሳላችሁ፡፡ ከክርስቶስ መመለስ በኋላ

በሚመጣው፣ በአዲሱ ዓለም፣ ጨዋማው ባህር ከምድር ጨርሶ ይወገዳል በምትኩም ሕይወት ሰጪ ንፁህ ውሃ ይተካል፡፡ የክርስቶስ ሥራ በዘፍጥረት 1 ከተከናወነው የመፍጠር ሥራ ጋር ተመሳሳይ ነው፣ እግዚአብሔር ግን በክርስቶስ ከዚያም ይዘልቃል፣ ፍጥረትንም ወደ ፍፃሜ ውበትና ሥርዓት ያመጣል፡፡ ፍጥረተ-ዓለሙ በጠቅላላ ወደ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርነት ይለወጣል፣ እግዚአብሔርና ህዝቡም በአዲሱ ዓለም በደስታ ይኖራሉ፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ ክርስቲያኖች በተደጋጋሚ ዘላለማዊ ተስፋቸውን ከፍጥረት ጋር ያነጣጥሉታል፡፡ አዲስ ኪዳን በግልፅ እንደሚያስቀምጥልን፣ የእኛ የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ በፍጥረት ሥራ ሰባተኛ ቀን ወደተደነገገው የሰንበት ዕረፍት መመለስ ነው፡፡ በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ለዘላለም እንኖራለን፡፡ በሙሴ ዘመን የእስራኤል ተስፋ ይኸው ነበር፣ ዛሬም የእኛ ተስፋ ይኸው ነው፡፡

የአዲስ ኪዳንን መመሪያ ስንከተል፣ የዘፍጥረትን የመከፈቻ የመጀመሪያ ምዕራፍ ከረጅም ዘመናት በፊት የተከናወነ ታሪክ ዘገባ ብቻ አድርገን አናነብበውም፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ የመጀመሪያ መምጣት የሚከናወነው ነገር፣ ዛሬ በየዕለቱ በእኛ ሕይወት እየሠራ ያለው ነገር እና አንድ ቀን ጌታ ተመልሶ ሲመጣ እግዚአብሔር ወደ ፍፃሜ የሚያመጣው ነገር ቅድመ ናሙናም ነው፡፡

በክርስቶስ መንግሥት በሦስቱም እርከኖች፣ በዓለምና በእኛም ሕይወት ውስጥ በወደቀው በኃጢአት ቀውስና ሞት ላይ እግዚአብሔር ዘምቶበታል፡፡ በመንግሥቱ ምሥረታ፣ በእድገቱና በፍፃሜው ዓለምን ወደ ከበረ ፍፃሜው ማለትም ለህዝቡ ወዳዘጋጀው አስደናቂ አዲስ ፍጥረት በሚያመራው ጎዳና ላይ አዋቅሯል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት አራት ዋና ሃሳቦችን ተመልክተናል፡፡ እነርሱም፡- የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ 11 ዋና ዓላማ፣ የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 አወቃቀርና ቀደምት ትርጉም፣ አዲስ ኪዳን የፍጥረትን መሪ ሃሳቦች ከክርስቶስ እና ከእኛ ሕይወት ጋር የሚያዛምድባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ በጥቂቱ ለመናገር ያህል፣ ሙሴ ስለ ፍጥረት ያቀረበውን ዘገባ በዚህ መንገድ መቅረባችን ለዚህ ዘመን ያለው አንድምታ እጅግ እየተደመምን እንድንመለከተው የሚያደርገን ነው፡፡

በዚህ ዘመን እንደሚኖር ክርስቲያን፣ ሙሴ በዘፍጥረት የነበረው ዓላማ እኛ በክርስቶስ ካለን ሕይወት ጋር እንዴት ሊዛመድ እንደሚችል ማየት ይገባናል፡፡ ልክ የዘፍጥረትን የመክፈቻ ምዕራፎች እንደሚያደምጡ እስራኤላውያን ሁሉ፣ እኛም በዚህ ኃጢአተኛ ዓለም ክርስቶስን በምንከተልበት ወቅት በቀላሉ ተስፋ የመቁረጥ ፈተና ያጋጥመናል፡፡ አንባቢዎቹ ወደ እግዚአብሔር እንከን የለሽ ዓለም እየተጓዙ እንደሆነ እንዲያምኑ በማድረግ እንዳበረታታቸው ሁሉ፣ እኛም በክርስቶስ ወደምንወርሰው ወደ እግዚአብሔር አስደናቂ ፍፁም ዓለም በምናደርገው ጉዞ ላይ ልንበረታታ ይገባናል፡፡